የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1395/2017

በገቢዎች ሚኒስቴር

የታክስ ከፋዮች ትምህርት ዳይሬክቶሬት

ነሐሴ, 2017 ዓ.ም

ሆሳዕና

መግቢያ

- በገቢ ግብር ሥርዓት ላይ ለውጥ በማድረግ የመንግስትን ገቢ አሰባሰብ ማሻሻል እና ለኢኮኖሚው እድገት እገዛ ማድረግ የሚቻል መሆኑ ስለታመነበት፤
- የታክስ ማስከፈያ መጣኔው ከወቅታዊው የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የሚያስችል ማስተካከያ ለማድረግ፤
- የታክስ መሰረቱን ለማስፋት እና ውጤታማ የሆነ የታክስ ማበረታቻ ስርዓት አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ፤
- ከታክስ ለመሸሽ የሚደረገውን ጥረት ለመከላከል በሚያስችል መንገድ የተወሰኑ የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ድንጋጌዎችን በማሻሻል የታክስ ስርዓቱ መሰረታዊ የታክስ መርሆችን ለማሳካት በሚያስከትል መልኩ እንዲቀረጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ አወጁ ተሻሽሏል፤

የማሻሻያው ዓላማዎች

የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ የሚከተሉት ሰባት ዓላማዎች ያሉት ሲሆን፡-

1) ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል የሚያርፍበትን የግብር ጫና መቀነስ፤(16,800)

2) የግብር መሰረትን ማስፋት፤

3) የግብር ስርዓቱ ላይ የሚታዩ የፍትሃዊነት ችግሮችን መቅረፍ፤

4) የአነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች የግብር አከፋፈል ስርዓት ቀላል እንዲሆን ማድረግ፤

5) ካፒታልን በማቀናጀት ለኢንቬስትመንት ተግባር ለማዋል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፤

6) የታክሱን መሰረት ለመሸርሸር እና ታክስ ለማጭበርበር በር የሚከፍቱ አሰራሮችን መከላከል፤

7) ግልጽነት በሚጎድላቸው አንቀጾች ምክንያት የሚፈጠረውን ውጣ ውረድን ማስቀረት፤

ማሻሻያ የተደረገባቸው አንቀጾች

የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008

እንደሚከተለው ተሻሽሏል

በአዋጁ የተሻሻሉ ዋና ዋና ድንጋጌዎች

- የግብር ከፋዮች ደረጃ ተሻሽሏል፡፡
- ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ ላይ ግብር መጣል ተጀምሯል፡፡
- የግብር መክፈያ ሰንጠረዦች ምጣኔ ተቀይሯል፡፡
- አማራጭ አነስተኛ ግብር መጣል(መሰብሰብ ተጀምሯል)፡፡
- በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ ግብይት ላይ ገደብ ተቀምጧል፡፡
- የደረጃ ለ ግ/ከፋዮች የግብር አወሳሰን ስርዓት ተቀይሯል፡፡
- የሠንጠረዥ መ ግብር መክፈያ ምጣኔዎች ተሻሽለዋል፡፡
- የተለያየ የንግድ ሥራ መስክ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ መረጃዎችን በተናጠል መያዝ አለበት፡፡
- የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዩች ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብቻ መሆኑ ቀርቷል፡፡
- በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት የተደነገገው ድንጋጌ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 2 ትርጉም

ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 27 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 28፣ 29 እና 30 ተጨምረዋል፦

- **ንዑስ አንቀጽ 28፡-** በጠቅላላ ሽያጭ ላይ የሚከፈል ግብር ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 (የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች የሚከፍሉት የገቢ ግብር) የተመለከቱት አነስተኛ ግብር ከፋዮች ከንግድ ስራቸው ባገኙት ዓመታዊ ጠቅላላ ሽያጭ ላይ ተሰልቶ ግብር የሚከፈልበት ቀለል ያለ የግብር ስርዓት ነው።

አንቀጽ 2 ትርጉም....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 29፡-** ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የቪዲዮ ማጋሪያ አገልግሎቶችን፣ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን፣ የድምጽ ማስተላለፊያ (ፖድካስት) አገልግሎቶችን እና የቀጥታ ስርጭት መድረኮችን ጨምሮ በኦንላይን መድረኮች ላይ ዲጂታል ይዘትን በመፍጠር እና በማሰራጨት የሚያገኘው ማንኛውም የገንዘብ ወይም በአይነት የሚገኝ ገቢ ነው። ይህም የሚከተሉትን ገቢዎች ያካትታል፦

ሀ) ማስታወቂያዎች እና ስፖንሰርሺፖች፣

ለ) የምርት ስም ስምምነቶች እና ድጋፎች፣ (**An Endorsement Agreement is a legally binding contract between your business and a public figure)**

ሐ) የአጋርነት ግብይት እና የምርት ምደባዎች፣(*ISO)*

አንቀጽ 2 ትርጉም.....ቀጠለ

መ) የደጋፊዎች አስተዋጽኦ፣ የገንዘብ ስጦታዎች ወይም የብዙሃን የገንዘብ ማሰባሰብ (ክራውድ ፈንዲንግ)፣

ሠ) የአባልነት ክፍያዎች፤

ረ) የዲጂታል ወይም የአካላዊ ሸቀጦች ሽያጭ፣

ሰ) ለማስተዋወቂያ እንቅስቃሴ ምትክ የተገኙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና

ሸ/ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች ክፍያዎች።

- **ንዑስ አንቀጽ 30፡-** የዲጂታል አገልግሎት ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን የዲጂታል ይዘት ያለው አገልግሎት ነው።

አንቀጽ 3 የግብር ከፋይ ደረጃዎች

የአዋጁ አንቀጽ 3 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡፡

- **ንዑስ አንቀጽ1፡-** ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የሚከተሉት የግብር ከፋይ ደረጃዎች ይኖራሉ፤

ሀ) የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፤

- ድርጅት (ህጋዊ ሰውነት መብት ያለው)፤ ወይም
- ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ብር 2 ሚሊዮን (ሁለት ሚሊዮን ብር) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው (ግለሰብ ነጋዴ)፤

ለ) ደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 2 ሚሊዮን (ሁለት ሚሊዮን ብር) የሚያንስ ሰው (ግለሰብ ነጋዴ) ነው፡፡

የቀድሞ አዋጅ				አዲሱ አዋጅ		
	ደረጃ ሐ	ደረጃ ለ	ደረጃ ሀ		ደረጃ ለ	ደረጃ ሀ
የግብር አወሳሰን	በግምት(በቁርጥ ግብር)	በሂሳብ መዝገብ	በሂሳብ መዝገብ	የግብር አወሳሰን	በግምት(ሽያጭን መሰረት በማድረግ)	በሂሳብ መዝገብ
የግብይት ሁኔታ	ያለደረሰኝ	በደረሰኝ	በደረሰኝ	የግብይት ሁኔታ	ያለደረሰኝ	በደረሰኝ
የታክስ አከፋፈል	ቲኦቲ	ቲኦቲ	ቫት	የታክስ አከፋፈል	ምንም	ቫት
የታክስ መክፈያ ወቅት	ከሐምሌ 1-30	ከሐምሌ 1-Èጉሜ 5/6	ከሐምሌ 1-ጥቅምት 30	የታክስ መክፈያ ወቅት	ከሐምሌ1-30	ከሐምሌ1-ጥቅምት 30(በየሩብ ዓመቱ)
ዓመታዊ ገቢ	እስከ 500 ሺህ	ከ500,001-1,000,000	ከ1,000,000 በላይ		እስከ 2,000,000	ከ2,000,000 ብር በላይ

አንቀጽ 3 የግብር ከፋይ ደረጃዎች….የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 2፡-** የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበውን የግብር ማስታወቂያ ወይም የሚያገኘውን ሌላ ማናቸውም መረጃ መሠረት በማድረግ ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ደረጃ የተለወጠ መሆን አለመሆኑን ይወስናል፡፡
- **ንዑስ አንቀጽ 3፡-** ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን እና ግብር ከፋዮችን የደረጃ "ሀ" ወይም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ብሎ ለመመደብ የሚያስችለውን ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ መጠን በኢኮኖሚ ጥናት ላይ በመመስረት ቢያንስ በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ ማሻሻል አለበት፡፡

አንቀጽ 4 በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት

የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ)(183 ቀን) እና 3(የግንባታ ስራ183 ቀን) ተሽረው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) እና 3 ተተክተዋል፦

- **ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ)፡-** ማናቸውም ሰው ተቀጣሪዎችን ወይም ሌሎች ሰራተኞችን በመመደብ የቴክኒክ አገልግሎት እና የምክር አገልግሎትን ጨምሮ የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት፤ አገልግሎቱ ወይም ተያያዥ የሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወነው የንግድ ስራ በአንድ የግብር ዓመት ወይም በማናቸውም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ድምር ከ91 (ዘጠና አንድ) ቀናት በላይ የተከናወነ ከሆነ፤(በቀድሞ አዋጅ 183 ቀን)

አንቀጽ 4 በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት….የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 3፡-** የግንባታ ስራው የሚከናወንበት ቦታ፤ ፕሮጀክቱ ወይም የስራ እንቅስቃሴው በአንድ የግብር ዓመት ወይም በማናቸውም አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ91 (ዘጠና አንድ) ቀናት በላይ የሚቆዩ እስከሆነ ድረስ የህንጻ ግንባታው የሚከናወንበት ቦታ ወይም የኮንስትራክሽኑ ስራ፤ የመገጣጠሚያው ወይም የተከላው ፕሮጀክት ወይም ከእነዚህ ጋር የተያያዙ የቁጥጥር ስራዎች በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት እንደሆኑ ይቆጠራል።

አንቀጽ 4 በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት.....የቀጠለ

ከአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 5 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 ተጨምሯል።

- **ንዑስ አንቀጽ 6፡-** ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የቴክኒክ አገልግሎት" ማለት የቴክኒክ፣ የአስተዳደር ወይም የምክር አገልግሎት ባህሪ ያላቸውን አልግሎቶችን የሚያካትት ሲሆን፤ የሚከተሉትን ይጨምራል፦

  ሀ) የሂሳብ አያያዝ፤

  ለ) የኦዲት፤

  ሐ) የኢኮኖሚና፤

  መ) የፋይናንስ፤

  ሠ) የህግ፤

አንቀጽ 4 በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት….የቀጠለ

ረ) የአስተዳደር፣

ሸ) የአርክቴክቸር፣

ቀ) የቅየሳ፣

በ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፤

ሰ) የኢንጂነሪንግ፣

ተ) ማህበራዊ ጉዳይ፣ ወይም

በሌላ ተመሳሳይ መስክ የሚሰጥ የሙያ አገልግሎት

አንቀጽ 6 የገቢ ምንጭ

ከአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 ተጨምሯል።

- **ንዑስ አንቀጽ 6፡-** በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የዲጂታል አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የተገኘ ገቢ እንደሆነ ይቆጠራል"

አንቀጽ 11 በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ መጣኔዎች

የአዋጁ አንቀጽ 11 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 11 ተተክቷል፦

- በመቀጠር በሚገኝ ወርሃዊ ገቢ ላይ ለሚጣለው ግብር ተፈጻሚ የሚሆኑት መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፦

በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ (ብር)	በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን መጣኔ	ተቀናሽ መጠን
0 ------------2,000	0%	0
2,001--------4,000	15%	300
4,001--------7,000	20%	500
7,001--------10,000	25%	850
10,001------14,000	30%	1,350
ከ14,000 በላይ	35%	2,050

የክፍል ሥራ

- ደመወዝ 9,000
- ደመወዝ 1,800 ብር
- የሥራ ግብር ?

- የአመት ፍቃድ፣ቦነስ እና ጉርሻ አሰላል፣
- የትርፍ ሰዓት ክፍያ አሰላል

ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ የታክስ ስሌት

- **<u>የጉርሻ/ቦነስ ታክስ አከፋፈል፡-</u>**

<u>ምሳሌ</u>፡-2 አቶ አየለ በXYZ ካምፓኒ የድርጅቱ ሲኒየር አካውንታት ሆነው ተቀጥረዋል ። ድርጅቱ በወር 15,600 ብር ደመወዝ የሚከፍላቸው ሲሆን በ2017 ዓ.ም ባሳዩት ውጤታማ የስራ አፈጻጸም የወር ደሞወዛቸውን በዓመቱ መጨረሻ በቦነስ መልክ ቢከፍላቸው አቶ አየለ ካገኙት ቦነስ ላይ መክፈል የሚጠበቅባቸው የስራ ግብር ስንት ነው?

ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ የታክስ ስሌት

<u>መልስ</u>

15,600*35/100 -1500 = 3,960

15,600/12= 1,300 +15,600 = 16,900.00

16,900*35/100 -1500= <u>4,415</u>

4,415 – 3,960 = <u>455</u>

455*12 = 5,460 የቦነስ የስራ ግብር ተከፋይ ይሆናል

አንቀጽ 14 የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔዎች

የአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፦

- **ንዑስ አንቀጽ 2**፡- **በግለሰቦች ኪራይ** ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፤-

መታዊ ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ (በብር)	የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ	ተቀናሽ መጠን
0-----------------24,000	0%	0
24,001---------48,000	15%	3,600
48,001---------84,000	20%	6,000
84,001--------120,000	25%	10,200
	30%	16,200
ከ168,000 በላይ	35%	24,600

አንቀጽ 15 ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ

ከአዋጁ አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 7 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 8 ተጨምሯል፦

- **ንዑስ አንቀጽ 8:-** ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም **"ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ"** ማለት ለማናቸውም አገልግሎት ከሚውል ህንፃ፣ ከመኖሪያ ቤት፣ ለመጋዘን አገልግሎት ከሚውል ህንፃ ኪራይ የሚገኝ ገቢ ሲሆን የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የሚገነባቸውን የኢንዱስትሪ መሰረተ-ልማቶች እና በካፒታል በዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ መሠረት የንግድ ስራ ሀብት ሆነው የሚከራዩ ህንፃዎችን ወይም ግሪን ሃውስ እና በመጋዘን ውስጥ ዕቃ የሚያከማቹ ሰዎች የሚከፍሉትን ክፍያ አይጨምርም።

አንቀጽ 19 በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ መጣኔዎች

የአዋጁ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 2 ተተክቷል እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀፅ (3) እና (4) ተጨምሯል፡፡ የቀድሞው ንዑስ አንቀፅ (3) እና (4) ንዑስ አንፅ (5) እና (6) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

- **ንዑስ አንቀጽ 2፡- የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮችን ሳይጨምር** በግለሰብ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ከንግድ ስራ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በአመት	የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔ	ተቀናሽ መጠን
0--------------24,000	0%	0
24,001--------48,000	15%	3,600
48,001--------84,000	20%	6,000
84,001--------120,000	25%	10,200
120,001------168,000	30%	16,200
ከ168,000 በላይ	35%	24,600

አንቀጽ 19 በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ መጣኔዎች.....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 3፡-** በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር እና በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ በማንኛውም የህግ ቅርጽ ቢቋቋምም በድርጅት ደረጃ የሚያገኘው ገቢ ግብር አይከፈልበትም፡፡
- ሆኖም ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር ለአባላቱ በሚያከፋፍለው ገቢ ላይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ስር ባለው ሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብሩን ቀንሶ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
- የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ለባለአክሲዮኖች ከሚያከፋፈለው ትርፍ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 57 መሰረት የትርፍ ድርሻ ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ዝርዝር አፈፃፀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

- በአዲሱ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 221 መሰረት **ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና** ማኅበር ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሙያና ለሙያው ደጋፊ የሆነ አገልግሎት (professional and complementary service) ለመስጠት የሚያቋቁሙት የማህበርተኞቹ ኃላፊነት በመዋጮዋቸው **የተወሰነ** የንግድ ማኅበር ነው።

- የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013
- የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች፣ የተወሰነ ሀላፊነት ያላቸው የሽርክና ማህበሮች ወይም ባለስልጣኑ በጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስር መካተት አለባቸው ብሎ የሚወስናቸው ሌሎች በንግድ ህጉ የተደነገጉ አደረጃጀቶችና አወቃቀሮች የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ እንላቸዋለን።
- A Collective Investment Scheme (CIS) is **a type of investment vehicle, which gives investors the opportunity to invest in the stock market without directly owning stocks and shares**

አንቀጽ 19 በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ መጣኔዎች....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 4፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢንቨስትመንት ፈንድ ድርጅቱ እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበሩ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ሌሎች ግዴታዎች ተፈፃሚ ይሆንባቸዋል።

የተጨመሩ አዲስ አንቀፆች 22 እና 23

- ከአዋጁ አንቀጽ 21 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ 22 እና 23 ተጨምረዋል፡፡
- አዲስ አንቀጽ 22 እና 23 በመግባቱ ምክንያት በነባሩ አዋጅ ከአንቀጽ 22 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች በቅደም ተከተል ከአንቀጽ 24 በመጀመር ተሸጋሽገዋል፡፡

አንቀጽ 22 ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ

- **ንዑስ አንቀጽ 1፡-** ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካሟላ የንግድ ገቢ ተደርጎ ይወሰዳል፦

  ሀ/ ትርፍ ለማግኘት ታስቦ በመደበኛነት የሚከናወን ከሆነ፤

  ለ/ ፈጣሪው ድርጅት ከሆነ፤ እና

  ሐ/ የሂሳብ መዝገብ የሚያዙ ከሆነ ወይም ከንግድ ጋር የተያያዙ ወጪዎች ተቀናሽ የሚደረጉለት ከሆነ።

- **ንዑስ አንቀጽ 2፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት ሁኔታዎች ካልተሟሉ፣ ገቢው እንደ ሌላ ገቢ ተመድቦ በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር የሚጣልበት ሲሆን ዝርዝር አፈፃፀሙ የሚኒስተሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

አንቀጽ 22 ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 3፡-**የታክሱ ባለሥልጣን የዲጂታል ይዘት ፈጠራ የንግድ እንቅስቃሴ መሆኑን ለመወሰን መመሪያዎች ያወጣል፤ በተለይም የገቢውን መጠን፣ የግብይቶችን ብዛት፣ የይዘቱን ዓይነት እና የንግድ ዓላማውን ከግምት ውስጥ ያስገባል።
- **ንዑስ አንቀጽ 4፡-** በኢትዮጵያ ለሚኖሩ ዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች ክፍያዎችን የሚያመቻች ማንኛውም የኦንላይን መድረክ፣ ዓመታዊ ገቢያቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከሚወስነው ገደብ በላይ ከሆነ ለእያንዳንዱ ፈጣሪ ያገኙትን ጠቅላላ ገቢ በየዓመቱ ለታክሱ ባለስልጣን ሪፖርት ማድረግ አለበት።

አንቀጽ 22 ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 5፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በኦንላይን መድረክ ሪፖርት የተደረገም ይሁን ያልተደረገ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ማንኛውም ገቢን በተመለከተ፣ ገቢው በደረሰው ሰው በዓመታዊ የገቢ ግብር ማስታወቂያው ላይ መገለጽ አለበት።
- **ንዑስ አንቀጽ 6፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተወሰነው ገደብ በላይ ገቢ የሚያገኝ ዲጂታል ይዘት ፈጣሪ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማግኘት እና ሁሉንም ተፈጻሚነት ያላቸውን የግብር ግዴታዎችን መወጣት አለበት።

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር

- **ንዑስ አንቀጽ 1፡-** በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ወይም በሌላ ማናቸውም ህግ የተደነገገው ቢኖርም፤ ማናቸውም ድርጅት ወይም ሰው ግብር በሚወሰንበት የግብር ዓመት ከሁሉም የንግድ ስራ የገቢ ምንጮች ባገኘው ትርፍ ላይ ሊከፍል የሚገባው ግብር በዚሁ የግብር ዓመት ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ከ2.5% (ከሁለት ነጥብ አምስት በመቶ) በታች ከሆነ ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር መክፈል አለበት።

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር...የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 2፡-** በዚህ አንቀጽ መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር የሚከፈለው በሚከተለው የማስከፈያ መጣኔ ይሆናል፦

  ሀ) የማናቸውም ድርጅት ወይም ሰው አመታዊ ጠቅላላ ገቢ 2.5%፤ ወይም

  ለ) ባንኮችን በሚመለከት ከባንክ ስራ የተገኘ የተጣራ ገቢ 2.5%፤

  ሐ) የኢንሹራንስ ኩባንያዎችን በሚመለከት ከህይወት እና ከህይወት ውጪ ከሆነ ኢንሹራንስ የተገኘው ጠቅላላ አረቦን 2.5%፤

  መ) ዋጋቸው የተወሰነ ዕቃዎችን አቅራቢ ሰው ወይም ድርጅትን በሚመለከት የኮሚሽን ገቢው 2.5%፤

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር...የቀጠለ

- ዓመታዊ ገቢ - ዓመታዊ ወጪ = የተጣራ ትርፍ (Taxable Income)
- 10,000,000- 8,000,000 = 2,000,000
- ግብር (2,000,000 x 30% = 600,000) (ድርጅት)
- ግብር (2,000,000 x 35% - 24,600 = 675,400) (ግለሰብ)
- አማራጭ አነስተኛ ግብር 10,000,000 x 2.5% = 250,000 ብር

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር...የቀጠለ

- ዓመታዊ ገቢ - ዓመታዊ ወጪ = የተጣራ ትርፍ (Taxable Income)
- 10,000,000- 9,500,000 = 500,000
- ግብር (500,000 x 30% = 150,000) (ድርጅት)
- ግብር (500,000 x 35% - 24,600 = 150,400) (ግለሰብ)
- አማራጭ አነስተኛ ግብር 10,000,000 x 2.5% = 250,000 ብር

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 3፡-** በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለው አማራጭ አነስተኛ ግብር በአዋጁ አንቀጽ 18 መሰረት ከሚከፈለው የንግድ ትርፍ ግብር ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
- **ንዑስ አንቀጽ 4፡-** የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በአዋጁ አንቀጽ 49 (በተሻሻለው አንቀጽ 50) መሰረት በጠቅላላ ገቢው ላይ ግብር በሚከፍል ግብር ከፋይ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡(የደረጃ ለ ግብር ከፋዮች የግብር አከፋፈል)

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 5፡-** በዚህ አንቀጽ መሰረት ግብር ከፋዩ የከፈለው ግብር ሊከፍል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ላይ የሚቀነሰው በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፦

  ሀ) እስከ 5 (አምስት) ዓመታት ድረስ፤

  ለ) በአዋጁ አንቀጽ 18 መሰረት ሊከፈል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር ላይ የሚቀነሰው ሂሳብ በዚህ አንቀጽ መሰረት ሊከፈል እስከሚገባው አማራጭ አነስተኛ ግብር ድረስ ሆኖ፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የተከፈለውን ተቀናሽ የተደረገበት የንግድ ትርፍ ግብር ሳይጨምር ይሆናል።

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር…የቀጠለ

- ዓመታዊ ገቢ - ዓመታዊ ወጪ = የተጣራ ትርፍ (Taxable Income)(2017 በጀት ዓመት)
- 10,000,000- 9,500,000 = 500,000
- ግብር (500,000 x 30% = 150,000) (ድርጅት)
- አማራጭ አነስተኛ ግብር 10,000,000 x 2.5% = 250,000 ብር ብናስከፍለውና ግብር ከፋዩ ከላይ የገለጸው ገቢና ወጪ ትክክል መሆኑ ከተረጋገጠ ብር 100,000 ከሚቀጥለው ዓመት የሚካካስ ግብር ይኖረዋል ማለት ነው።
- ዓመታዊ ገቢ - ዓመታዊ ወጪ = የተጣራ ትርፍ (Taxable Income) (2018 በጀት ዓመት)
- (ምሳሌ 1)
- 10,000,000 - 8,000,000 = 2,000,000
- ግብር (2,000,000 x 30% = 600,000) (ድርጅት)
- አማራጭ አነስተኛ ግብር 10,000,000 x 2.5% = 250,000 ብር ልየነት 350,000
- በበጀት ዓመቱ ከአማራጭ አነስተኛ ግብር በላይ ለመክፈል ስለመጣ (ትርፋማ ስለሆነ) የ2017 በጀት ዓመትን ብር 100,000 በመቀነስ ቀሪውን 500,000 ብቻ እናስከፍለዋለን ማለት ነው።
- 10,000,000 – 9,100,000 = 900,000 (ምሳሌ 2)
- 900,000 x 30% = 270,000 በ2017 በጀት ዓመት በአማራጭ አነስተኛ መሰረት የከፈለው ብር 20,000 ይቀናነስለታል ቀሪው ብር 80,000 ይሸጋገራል።

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር….የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 6፡-** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሚከተሉት ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነጻ ተደርገዋል፦

  ሀ) በኪሳራ ምክንያት መፍረስ ላይ ያለ ድርጅት፤ እና

  ለ) በእዳ ማሽጋሸግ ላይ ያለ ድርጅት።

- **ንዑስ አንቀጽ 7፡-** የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ህግ መሰረት የግብር እፎይታ በተሰጠው ሰው ላይም ተፈጻሚ ይሆናል። ስለሆነም አማራጭ አነስተኛ ግብሩ የተሰጠው ማበረታቻ ተቀንሶ ሊከፈል በሚገባው የገቢ ግብር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር….የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ 8፡-** ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፦

ሀ) **"አመታዊ ጠቅላላ ገቢ"** ማለት በግብር አመቱ ከተከናወነ የዕቃ ሽያጭ እና አገልግሎት የመስጠት ተግባር የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ነው።

ለ) **"ከባንክ ስራ የተገኘ ገቢ"** ማለት ከሚከተሉት ምንጮች የተገኘ ገቢ ነው፦

(I) ብድርን ከመሳሰሉት የባንኩ ሃብቶች በሚገኝ ወለድ እና ተቀማጭ ሂሳብን ለመሳሰሉት የባንኩ እዳዎች በሚከፈል ወለድ መካከል ያለው ልዩነት፤

(II) ግብይትን፤ ሂሳብ ማስተዳደርን እና የምክር አገልግሎትን ከመሳሰሉ አገልግሎቶች የሚገኝን ገቢ ጨምሮ ከክፍያዎች እና ከኮሚሽኖች የሚገኝ ገቢ፤

(III) በፋይናንስ ሰነዶች በመገበያየት የሚገኝ ትርፍ እና የሚያጋጥም ኪሳራን ጨምሮ ከግብይት የሚገኝ የተጣራ ገቢ፤

(IV) ለግብይት ወይም ለኢንቨስትመንት አላማ ከተያዙ የፋይናንስ ሰነዶች የሚገኝ ጠቅላላ ገቢ፤ እና

(V) አስቀድሞ ከሂሳብ መዝገብ የተሰረዙ ሂሳቦችን ከማስመለስ እና ከመሳሰሉት የተለያዩ ገቢዎች የተገኘ የሌሎች የስራ እንቅስቃሴዎች ገቢ።

አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር….የቀጠለ

ሐ) **"የኮሚሽን ገቢ"** ማለት በህግ ወይም በተዋዋዮች መካከል በተደረገ ውል በተወሰነው መሰረት ከአንድ ዕቃ ወም አገልግሎት ዋጋ ላይ ለአገልግሎት ሰጪው የሚከፈል ገንዘብ ነው።

መ) **"ዋጋው የተወሰነ ድርጅት"** ማለት ዕቃዎችን የሚሸጥበት ወይም አገልግሎትን የሚያቀርብበት ዋጋ በውል ወይም በመንግስት አካል የተወሰነ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ድርጅት ነው።

አንቀጽ 24/26 ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች

የአዋጁ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀፅ (1) (ለ) እና (2) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀፅ (1) (ለ) እና (2) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፅ (1) (ለ) እና (2) ተተክተዋል፦

- **ንዑስ አንቀፅ (1) (ለ)፡-**የፌዴራል መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም የክልል መንግስት ካቢኔ ባደረገው ጥሪ መሰረት የአገሪቱን አንድነት እና ሉዓላዊነትን ለማስከበር ወይም ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ወይም ወረርሽኝ ለመከላከል ለተመሳሳይ ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት ወይም የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለተዘረዘሩ ማህበራዊ ስራዎች የሚውል ከሆነ ነው።

አንቀጽ 24/26 ለበጎ አድራጎት ዓላማ ....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀፅ (2) ፡-** በዚህ አንቀጽ መሰረት ለግብር ከፋዩ የሚፈቀደው ጠቅላላ ተቀናሽ ከግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ 10% (አስር በመቶ) መብለጥ የለበትም። ሆኖም የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለተወሰኑ መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች የሚደረገው ድጋፍ ከዚህ መጠን ከፍ እንዲል ሊፈቅድ ይችላል።

ለበጎ አድራጎት ዓለማ የሚደረጉ ስጦታዎች

የቀጠለ

- በአዋጁ መሰረት ለበጎ አድራጎት ስራ የሚደረጉ ስጦታዎች የሚፈቀደው ተቀናሽ ወጪ ከታክስ ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ ከ 10 በመቶ የማይበልጥ ሆኖ "ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ" ማለት ለበጎ አድራጎት ስራ የተደረጉት ስጦታዎችን ሳይቀነስ ነው።

ምሳሌ፡- የግብር ከፋዩ ዓመታዊ ገቢ 1,200,000 ብር ቢሆንና

- በግብር ዓመቱ በህጉ የተፈቀዱ የተለያዩ ወጪዎች ብር 800,000 ቢቀናነስለት፤
- በሕግ ለተፈቀደለት ድርጅት የተሰጠ የበጎ አድራጎት ስጦታ ብር 150,000 ሰጥቻለሁ በማለት መረጃ ቢያቀርብ፤
- በሕጉ መሰረት ግብር ከፋዩ የሰጠው ስጦታ እንደወጪ የሚያዝለት ስንት ብር ነዉ?

አንቀጽ 27/29 ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች እና ኪሳራዎች

ከአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል (ነ) በተሸጋገረው አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል (ነ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል (ኘ) ተጨምሯል፡፡

- **ንዑስ አንቀጽ (1)(ኘ)፡-** ማናቸውም ግብር ከፋይ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ ቼክ፤ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ የባንክ ድራፍት፤ ከአንድ የባንክ ሂሳብ ወደሌላ የባንክ ሂሳብ እና ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የክፍያ መፈፀሚያ መንገዶች ገንዘብ ከማስተላለፍ ውጪ በአንድ ቀን ውስጥ ለአንድ ሰው ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ በሆነ ጥሬ ገንዘብ የፈጸመው ወይም የፈጸማቸው ክፍያዎች፤(ምሳሌ ህንድ)

አንቀጽ 33 ለደረጃ ለ ግ/ከፋዮች
ቀላል የታክስ ሥርዓት

የአዋጁ አንቀጽ 33 ተሰርዟል።

አንቀጽ 49/50 የደረጃ “ለ” ግ/ከፋዮች ግብር አከፋፈል

የአዋጁ አንቀጽ 49 ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ 50 ተሸሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 50 ተተክቷል፦

- **አንቀጽ 50:- የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል**
  - **ንዑስ አንቀጽ (1)፦** በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ወይም በሌላ የታክስ ህግ የተደነገገው ቢኖርም የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዩች ግብር የሚከፍሉት በጠቅላላ ገቢያቸው ላይ ይሆናል።
  - **ንዑስ አንቀጽ (2)፦** ግብሩ የሚጣለው እና የሚከፈለው በግብር ዓመቱ ውስጥ ከዕቃ እና ከአገልግሎት ሽያጭ በሰበሰቡት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ላይ ነው።

አንቀጽ 49/50 የደረጃ “ለ” ግ/ከፋዮች ግብር አከፋፈል…… የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለው ግብር ማስከፈያ መጣኔ የሚከተለው ይሆናል፡-

ግብር የሚከፈልበት አመታዊ ጠቅላላ ገቢ	መጣኔ (በመቶኛ)
0 – 100,000	2%
100,001 – 500,000	3%
500,001 – 1,000,000	5%
1,000,001 – 1,500,000	7%
1,500,001 – 2,000,000	9%

አንቀጽ 49/50 የደረጃ “ለ” ግ/ከፋዮች ግብር አከፋፈል......የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለው ግብር ማስከፈያ መጣኔ የሚከተለው ይሆናል፦

ግብር የሚከፈልበት አመታዊ ጠቅላላ ገቢ	መጣኔ (በመቶኛ)
0 – 100,000	2%
100,001 – 500,000	3%
500,001 – 1,000,000	5%
1,000,001 – 1,500,000	7%
1,500,001 – 2,000,000	9%

- ምሳሌ፡- በቀድሞ አሰራር 1 የደረጃ ሀ/ለ በሆቴል ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ግብር ከፋይ ዓመታዊ ገቢ ብር 1,600,000 ቢገመትበት።
- ግብር የሚከፈልበት ገቢ 1,600,000 x 25% = 400,000
- ግብር 400,000 x 35% -18,000 = 122,000 ግብር ይከፍላል።
- ተርን ኦቨር ታክስ 1,600,000 x 2% = 32,000 ድምር 154,000 ብር ግብር እና ተርን ኦቨር ታክስ ይከፍላል።በአዲሱ አሰራር 1,600,000 x 9% = 144,000 ልዩነት 10,000 ብር
- አልጋ ማከራየት ብቻ ቢሆን 1,600,000 x 26% = 416,000 x 35% -18,000 = 127,600 ግብር
- ተርን ኦቨር ታክስ 1,600,000 x 10% = 160,000 ድምር 287,600 ልዩነት 143,600

አንቀጽ 49/50 የደረጃ “ለ” ግ/ከፋዮች ግብር አከፋፈል.....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (4)፡-** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ **ለሚከተሉት ተፈጻሚ አይሆንም፡-**

ሀ) የሚከተሉትን ጨምሮ የሙያ አገልግሎት ለሚሰጡ ሰዎች፡-

1) ለሂሳብ አያያዝ ሙያ፤
2) ለአርኪቴክቶች፤
3) ለአማካሪዎች፤
4) ለግንባታ ስራ ተቋራጮች፤
5) ለመሃንዲሶች፤
6) ለፋይናንስ፣ ለኢኮኖሚ እና ኢንቨስትመንት ባለሙያዎች፤
7) ለጤና ባለሙያዎች፤
8) ለህግ ባለሙያዎች፤

ለ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች፤ እና

ሐ) የሂሳብ መዝገብ በማቅረብ በሠንጠረዥ “ሐ” መሰረት በተጣራ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ላይ ግብር ለመክፈል **ለመረጡ** የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች፤

አንቀጽ 49/50 የደረጃ “ለ” ግ/ከፋዮች ግብር አከፋፈል.....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (5)፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 4 በተዘረዘሩት ሙያዎች የተሰማሩ ግብር ከፋዮች በዚህ አዋጅ ለደረጃ “ሀ” የሚጠየቀውን የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው።
- **ንዑስ አንቀጽ (6)፡-** የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች በእያንዳንዱ የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚከፍሉት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው የግብር አከፋፈል ዘዴ ነው።

አንቀጽ 51/52 በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች ገቢ

የአዋጁ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፡-

- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር የሚከፍልበት መጣኔ፡-

ሀ) ጠቅላላ ክፍያ ላይ ለመድን በሚከፈል አረቦን 15% (አስራ አምስት በመቶ) እና የሮያልቲ 10% (አስር በመቶ)፤

ለ) በትርፍ ድርሻ በጠቅላላ ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ)፤

ሐ) በወለድ ጠቅላላ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ)፤

መ) ከስራ አመራር ክፍያ ወይም ከቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ላይ ከጠቅላላ ገቢው 15% (አስራ አምስት በመቶ)፤

መድን ሕግ የመድን ውልን የሚዳኝ ሕግ ነው። የመድን ሕግ ብዙ ጥቅሞችን ያየዘና በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን ሊጠቅሙ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮችን አካቶ የሚይዝ ነው። የመድን ውል በመድን ሰጪው (Insurer) እና በመድን ገቢው (Insured) መካከል የሚደረግ የሁለትዮሽ ውል ሲሆን መድን ሰጪው በውሉ ላይ "የተጠቀሰውን አደጋ በደረሰ ጊዜ በመድህን ገቢው ላይ የሚደርሰውን የምጣኔ ሀብት ኪሳራ በውሉ ላይ ከተጠቀሰው መጠን ሳይበልጥ የመካስ ግዴታን ሲቀበል መድን ገቢው በአንፃሩ በውሉ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ እና መጠን የመድን **መግቢያ ክፍያ (አረቦን)** ለመድን ሰጪው የመክፈል ግዴታን ይወስዳል።

አንቀጽ 53 የዲጂታል አገልግሎት ግብር

የአዋጁ አንቀጽ 51 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 52 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 53 ተጨምሯል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፦** በኢትዮጵያ ውስጥ የዲጂታል አገልግሎትን በማቅረብ ገቢ የሚያገኝ ነዋሪ ወይም ነዋሪ ያልሆነ ማንኛውም ሰው የሚያገኘው ገቢ ግብር ይከፈልበታል።
- **ንዑስ አንቀጽ (2)፦** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚከፈለው ግብር ከ5% (አምስት በመቶ) የማይበልጥ ሲሆን የማስከፈያው መጣኔ፣ የአከፋፈሉ ሁኔታ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

አንቀጽ 53/55 በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪዎች ግብር

የአዋጁ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል፡-

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** በኢትዮጵያ በሚካሄድ የመዝናኛ አገልግሎት ተሳታፊ የሆነ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ወይም ቡድን ከመዝናኛ አገልግሎት በሚያገኘው ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፍላል።

አንቀጽ 54/56 ሮያሊቲ

የአዋጁ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተተክቷል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው የሮያልቲ ገቢ ያገኘ እንደሆነ፤-

  ሀ) በጠቅላላ የሮያልቲ ክፍያ ላይ 10% (አስር በመቶ)፤ ወይም (ኬንያ 15% ታንዛኒያ 20%)

  (ሮያልቲ ማለት፡-ማንኛውንም የሥነ-ጽሑፍ፣ የሥነ-ጥበብ ወይም የሳይንሳዊ ሥራ የቅጂ መብት፣ማንኛውንም የፈጠራ ባለቤትነት መብት፣ ፈጠራ፣ የንግድ ምልክት፣ ንድፍ ወይም ሞዴል፣ ፕላን፣ የሚስጥር ቀመር...ወዘተ)

  ለ) የሮያልቲ ገቢው የተገኘው ከኪነጥበብ ወይም ከባህላዊ ስራ ከሆነ 5% (አምስት በመቶ)፤ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሮያልቲ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላ የሮያልቲ ገቢው ላይ 10% (አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 55/57 የትርፍ ድርሻ

የአዋጁ አንቀጽ 55 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 57 ተሸሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 57 ተተክቷል፡-

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነና የትርፍ ድርሻ ያገኘ ሰው በጠቅላላ የትርፍ ድርሻ ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የትርፍ ድርሻ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።
- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ የትርፍ ድርሻ ገቢ ሲያገኝ በጠቅላላ የትርፍ ድርሻ ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የትርፍ ድርሻ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 55/57 የትርፍ ድርሻ....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ላቋቋመው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ወይም የኩባንያዎች ቡድን አባል ለሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ለሆነ ድርጅት የአክሲዮን ድርሻ ያከፋፈለ እንደሆነ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 ድንጋጌዎች በድርጅቱ ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።
- **ንዑስ አንቀጽ (4)፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ከተከፋፈለው ሃብት ጋር በተያያዘ የሚፈቀድ ወይም ተቀናሽ የሚደረግ ወጪ የሌለ ሲሆን፤ ግብር ከፋዩ የተከፋፈለውን ገንዘብ ማስተካት ወይም ማካካስ ወይም ገንዘቡ በተላለፈበት አመት ይህንን ሂሳብ በግብር አመቱ የግብር ከፋዩ ገቢ ውስጥ ማካተት የለበትም።

አንቀጽ 55/57 የትርፍ ድርሻ.....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (5)፦** ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የኩባንያዎች ቡድን" ማለት አንድ ኩባንያ (ከዚህ በኋላ "ተቆጣጣሪው የቡድኑ ኩባንያ" እየተባለ የሚጠራው) በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች (ከዚህ በኋላ "በቁጥጥሩ ስር ያሉ ኩባንያዎች" ተብለው በሚጠሩት) ውስጥ 50% (ሃምሳ በመቶ) እና ከዚያ በላይ ያሉ አክሲዮኖች ያሉት እንደሆነ ነው።

አንቀጽ 56/58 ወለድ

የአዋጁ አንቀጽ 56 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 58 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 58 ተተክቷል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፦** በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው የወለድ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ) ግብር ይከፍላል።
- **ንዑስ አንቀጽ (2)፦** በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ የወለድ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ) ግብር ይከፍላል።

አንቀጽ 56/58 ወለድ.....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም አንድ የፋይናንስ ተቋም በሌላ የፋይናንስ ተቋም ገንዘብ በማስቀመጥ ወይም በሌላ ተያያዥ አገልግሎት የሚያገኘው ወለድ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል፡፡
- **ንዑስ አንቀጽ (4)፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ግብር ከፋይ ዕቃን ወይም አገልግሎትን በዱቤ በመሸጥ የሚያገኘው ወለድ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል፡፡

አንቀጽ 57/59 ከዕድል ሙከራ የሚገኝ ገቢ

የአዋጁ አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል፡-

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረጉ የዕድል ሙከራ ጨዋታዎች ተሳትፎ ገቢ ያገኘ ሰው ባገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 59/61 የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም

የአዋጁ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ (2)፤ (3) እና (7) በተሸጋሸገው አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ (2)፤ (3) እና (7) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀፅ 61 ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3) እና (7) ተተክተዋል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በሚከፈለው ግብር ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው መጣኔ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ይሆናል።(ከዚህ በፊት ከሼር እና ቦንድ ላይ 30 በመቶ ነበር)

አንቀጽ 59/61 የካፒታል ንብረቶቹን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም.....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** ግብር የሚከፈልበትን ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ነው የሚባለው በሚከተለው ቀመር ተሰልቶ የሚገኘው ጥቅም ነው፡-

  ሐ - (ሀ + ሀxለ) = ግብር የሚከፈልበት ጥቅም

  ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፦

  ሀ - ሀብት የተፈራበት/የተገዛበት ዋጋ

  ለ - የዋጋ ንረት ማስተካከያ 30% (ሠላሳ በመቶ)

  ሐ - ሀብቱ የተላለፈበት ዋጋ

- **ንዑስ አንቀጽ (7)፡-** ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፦ **"ግብር የሚከፈልበት ሃብት"** ማለት አክሲዮን፣ ቦንድ እና ቤት ሲሆን፤ ቤትን በሚመለከት ቤቱ ከመተላለፉ በፊት ለሁለት አመታት ሙሉ በሙሉ ለመኖሪያነት ያገለገለ ህንጻን አይጨምርም።

አንቀጽ 59/61 የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም.....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** ግብር የሚከፈልበትን ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ነው የሚባለው በሚከተለው ቀመር ተሰልቶ የሚገኘው ጥቅም ነው፡-

  ሐ - (ሀ + ለ) = ግብር የሚከፈልበት ጥቅም

  ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፡-

  ሀ - ሀብት የተፈራበት/የተገዛበት ዋጋ (12,000,000)

  ለ - የዋጋ ንረት ማስተካከያ 30% (ሠላሳ በመቶ)

  ሐ - ሀብቱ የተላለፈበት ዋጋ (20,000,000 ብር)

- 20,000,000 - (12,000,000 + 12,000,000 x30%)
- 20,000,000 – (12,000,000 + 3,600,000)
- 20,000,000 – 15,600,000 = 4,400,000
- 4,400,000 x 15% = 660,000 ብር ግብር ይከፍላል

አንቀጽ 62 ከኢትዮጵያ ውጭ የሚፈጸም ቀጥተኛ ያልሆነ ዝውውር

ከአዋጁ አንቀጽ 59 ወይም ከተሸጋሸገው አንቀጽ 61 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 62 ተካቷል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፦** የማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ታክስ የሚከፈልበት ገቢ፤ ገቢው ከተገኘበት ቀን በፊት ባለው የ365 ቀናት ጊዜ ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተሳሰሩ ኩባንያዎች አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ጋር የተያያዘውን አክሲዮን ወይም የአባልነት መብት ዋጋ ከ20% በላይ በመሸጥ የተገኘውን ገቢ ይጨምራል።

tax haven in Seychelles

- The country has a territorial tax system, meaning it primarily taxes income generated within Seychelles, while foreign-sourced income for International Business Companies (IBCs) is exempt.
- **Zero tax on foreign income:** International Business Companies (IBCs) incorporated in Seychelles are exempt from taxes on income, capital gains, dividends, interest, and royalties earned outside the country.

አንቀጽ 61/64 ያልተከፋፈለ ትርፍ

የአዋጁ አንቀጽ 61 ወይም የተሸጋሸገው አንቀጽ 64 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 64 ተተክቷል፡-

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** በሚኒስትሩ በሚያወጣው *መመሪያ* መሰረት በአንድ የግብር ዓመት ግብር ከተከፈለ በኋላ ለአባላቱ ያልተከፋፈለ እና *መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ* የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፈልበታል፡፡
- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ያልተከፋፈለ ትርፍ" ማለት የኩባኒያው የሂሳብ ዓመት ካለቀ በኋላ ባሉት አስራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ ለባለአክሲዮኖች ያልተከፋፈለ ወይም የኩባኒያውን ካፒታል ለመጨመር ያልዋለ የተጣራ ትርፍ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ ለሚያካሂድ የውጭ አገር ኩባኒያ ያልተላከ ትርፍን ያካትታል፡፡

አንቀጽ 61/64 ያልተከፋፈለ ትርፍ....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ኩባንያ ትርፉን መልሶ ኢንቨስት እንዳደረገ የሚታሰበው፣ የተጣራ ትርፉን የባለአክሲዮኖቹን አክሲዮን እና የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ ሲጠቀምበት ነው።
- **ንዑስ አንቀጽ (4)፡-** ባለአክሲዮኖች የሚያገኙትን የትርፍ ድርሻ ቃል ለገቡት አክሲዮን መክፈያ በሚያውሉበት ጊዜ ሊደረግ የሚገባው ድጋፍ፣ አይነትና መጠን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

አንቀጽ 62/65 በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት የሚላክ ትርፍ

የአዋጁ አንቀጽ 62 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 65 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 65 ተተክቷል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ስራ የሚያከናውን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው በቋሚነት ከሚሰራ ድርጅት የሚላክለት ትርፍ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።
- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ትርፉን የግብር ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በ12 (አስራ ሁለት) ወራት ውስጥ ያልላከ ቢሆንም እንደላከ ተቆጥሮ ግብሩን እንዲከፍል ይደረጋል። ሆኖም ይህ ትርፍ ወደ ውጭ በሚላክበት ጊዜ በድጋሚ የሚከፈል ግብር አይኖርም።
- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** የዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የሚመራው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይሆናል።

አንቀጽ 65/68 ከገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ገቢ

ከአዋጁ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ (1) (ከ) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ 1 (ከ) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ነ)፤ (ኘ)፤ (አ) ተጨምረዋል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (1)**

  (ነ) የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ የሚሰበስበው አረቦን፤

  (ኘ) በስራ ላይ ያሉ ኩባንያዎች አዲስ ከሚያወጡት አክሲዮን የሚገኝ የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም (ፕሪሚየም)፤

  (አ) ማናቸውም ኩባንያ በኩባንያው ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከአስራ ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ (12.5%) ያላነሰ ድምጽ የመስጠት መብት እና የኩባንያውን ውሳኔዎች የመቆጣጠር መብት ላለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የሚፈጽመው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍያ፤”

አንቀጽ 81 ክፍያ የሚፈጸምባቸው ዘዴዎች

ከአዋጁ አንቀጽ 77 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 80 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 81 ተጨምሯል፤

- ንዑስ አንቀጽ (1) ፡- ማናቸውም ግብር ከፋይ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ በሚደረግ ቼክ፤ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ በሚደረግ የባንክ ድራፍት፤ ከባንክ ሂሳብ ወደ ባንክ ሂሳብ ገንዘብ በማስተላለፍ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የክፍያ መፈፀሚያ መንገዶች ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ግብይቶች ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብ መቀበል አይችልም፡፡

  ሀ) በአንድ ቀን ውስጥ ከአንድ ሰው ጋር በተደረገ ጠቅላላ ግብይት፤ ወይም

  ለ) ከአንድ ግብይት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ክፍያ፤ ወይም

  ሐ) ከአንድ ሰው ጋር ከተፈጸመ አንድ ግብይት ወይም ተግባር ጋር የተያያዘ ክፍያ፤

አንቀጽ 81 ክፍያ የሚፈጸምባቸው ዘዴዎች....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (2)** ፡- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

  ሀ) በመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ በመንግስት የልማት ድርጅቶች፤ በባንኮች እና በማይክሮ ፋይናንስ ድርጅቶች፤

  ለ) የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዘሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ወይም የተለዩ ግብይቶች፤

- **ንዑስ አንቀጽ (3)** ፡-ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ግብይት" ማለት ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ሰው የሚያከናውነው በዚህ አዋጅ መሰረት ግብር የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ነው።

- **ንዑስ አንቀጽ (4)** ፡- የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽል ይችላል።

አንቀጽ 82/86 መዝገብ ስለመያዝ

- **የአዋጁ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዟል።**
- **የአዋጁ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 3 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፦**
  - **ንዑስ አንቀጽ (3)** ፦ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 86(1) መሰረት የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይችላሉ። የያዙት የሂሳብ መዝገብ ተቀባይነት ካገኘ የሚከፍሉት ግብር የሚወሰነው በሂሳብ መዝገባቸው መሰረት ይሆናል።

አንቀጽ 82/86 መዝገብ ስለመያዝ ....የቀጠለ

የአዋጁ አንቀጽ **82** ንዑስ አንቀጽ **6** ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ **86** ንዑስ አንቀጽ **6** ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ **86** ንዑስ አንቀጽ **6** ተተክቷል፣ እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ **8፣9፣10** እና **11** ተጨምሯል፤

- **ንዑስ አንቀጽ (6)** ፦ በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግብር ከፋዩ አንድ ወጪ በተቀናሽነት እንዲያዝለት ወይም በአንድ ሀብት ዋጋ ውስጥ እንዲካተትለት የሚያስችለውን የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ወጪ በተቀናሽነት እንዲያዝ ወይም አንድ ወጪ በአንድ ሀብት ዋጋ ውስጥ እንዲካተት ላይፈቅድ ይችላል፡፡

አንቀጽ 82/86 መዝገብ ስለመያዝ ....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (8)፡-** ማንኛውም ግብር ከፋይ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊይዝ የሚገባውን የሂሳብ መዝገብ ካላቀረበ ግብሩ በግምት ይወሰናል። ሆኖም ለደረጃ "ለ" በተቀመጠው የማስከፈያ ዘዴ መሰረት ሊስተናገድ አይችልም።
- **ንዑስ አንቀጽ (9)፡-** ማንኛውም ድርጅት ግብር ከፋይ በሌላ ኩባንያ ውስጥ አክሲዮን ለመግዛት በተበደረው ገንዘብ ላይ የሚከፍለው ወለድ በወጪነት ይያዛል። ሆኖም የዚህ አይነቱ ወጪ ተቀናሽ የሚደረገው ድርጅቱ አክሲዮን ከገዛበት ድርጅት የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ የሚያገኝ ከሆነ ነው። ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።
- **ንዑስ አንቀጽ (10)፡-** ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር ወይም በሙያ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚያወጡት ወጪ ተቀናሽ የሚደረግበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

አንቀጽ 82/86 መዝገብ ስለመያዝ .....የቀጠለ

በአዋጁ ከአንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 7 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 7 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 86 ~~(8)~~ ተጨምሯል፤ የነባሩ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ (7) ንዑስ አንቀጽ 9 በሚል ተተክቷል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (~~8~~ ወይም 11)፡-** በሠንጠረዥ ‘ሐ’ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት እና ከአንድ በላይ የንግድ ሥራ መስክ ገቢ የሚያገኝ የደረጃ “ሀ” ግብር ከፋይ፣ በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለእያንዳንዱ የተለየ የሥራ መስክ የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ መረጃዎችን በተናጠል መያዝ አለበት፡፡(በጋራ የሚጠቀማቸው ንብረቶች ካሉ በአስተዋጸው ልክ ወጪው መካተት አለበት)

አንቀጽ 83/87 ግብርን ስለማሳወቅ

የአዋጁ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ(2) እና (3) ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ተተክተዋል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (2)፦** አንድ ተቀጣሪ በአንድ አመት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆነ ቀጣሪ ያለው ከሆነ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 በተመለከተው መሰረት በዚሁ አመት ውስጥ በሌላ ሰንጠረዥ ስር የሚወድቅ ገቢ ያለው ከሆነ ወይም ከራሱ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከሆነ፤ አመቱ በተጠናቀቀ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ የተጠቃለለውን ገቢውን ማስታወቅ አለበት።
- **ንዑስ አንቀጽ (3)፦** የተጠቃለለውን ገቢውን የማስታወቅ ግዴታ ለሌለበት ተቀጣሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96 መሰረት ቀጣሪው በየአመቱ የሚሰጠው ከተከፋዩ ሂሳብ ላይ ግብር መቀነሱን የሚያረጋግጠው ማስረጃ ለዚህ አዋጅ እና ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም ተቀጣሪው ለአመቱ ሊከፍል ለሚገባው ግብር በማስረጃነት የሚያገለግል ይሆናል።

አንቀጽ 88 አስተዳደራዊ መቀጫ

ከአዋጁ አንቀጽ 83 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 87 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 88 ተጨምሯል፤

- በዚህ አዋጅ አንቀጽ 81 የተደነገገውን በመተላለፍ በአንቀጹ ከተመለከተው መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተቀበለ ግብር ከፋይ በትርፍነት የተቀበለውን ገንዘብ እጥፍ አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፡፡

አንቀጽ 89 ግብርን ስለመክፈል

የአዋጁ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 ተተክተዋል፤ እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ 5 ተካቷል፡-

- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡፡

  ሀ) ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት ለግብር 25% (ሃያ አምስት በመቶ) የሂሳብ ሪፖርት ከሚያቀርቡበት ወር መጨረሻ ጀምሮ በሚቆጠር በየሶስት ወሩ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አስቀድመው ይከፍላሉ፤

  ለ) የሂሳብ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወር መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርቱ መሰረት ሊከፍሉ ከሚገባው ግብር ላይ በየሶስት ወሩ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን ይከፍላሉ፤

አንቀጽ 89 ግብርን ስለመክፈል.....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል።

ሐ) የሂሳብ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት የግብር ስሌት ሲከናወን በየሶስት ወሩ የከፈሉት ሊከፈል ከሚገባው የበለጠ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ በብልጫ የከፈሉት ሂሳብ ተመላሽ ይደረጋል። የተመላሹ ክፍያ የሚፈፀመው በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሰረት ለተመላሽ ተቀንሶ ከሚያዘው ሂሳብ ላይ ይሆናል።

መ) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለውን የቅድሚያ ግብር አፈፃፀም የሚወሰን መመሪያ ሚኒስትሩ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 89 ግብርን ስለመክፈል ....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (4)፡-** የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡፡

  ሀ) ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት የከፈሉትን ግብር 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ከሐምሌ ወር መጨረሻ ጀምሮ በሚቆጠር በየሦስት ወሩ በ30 (ሰላሳ) የስራ ቀናት አስቀድመው ይከፍላሉ፤

  ለ) በግብር ዓመቱ ሐምሌ ወር መጨረሻ ሊከፈሉ ከሚገባው ግብር ላይ በየሦስት ወሩ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን ይከፍላሉ፤

አንቀጽ 89 ግብርን ስለመክፈል ....የቀጠለ

- **ንዑስ አንቀጽ (5)፡-** በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 4 የተደነገገው ቢኖርም ለመጀመሪያ ጊዜ የገቢ ግብር የሚከፍሉ አዲስ ግብር ከፋዮች የመጀመሪያውን የግብር ዓመት በተመለከተ ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ነው፡-

  ሀ) የደረጃ “ሀ” አዲስ ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ገቢያቸውን ማስታወቅ ባለባቸው ጊዜ በግብር ዓመቱ ሊከፈል የሚገባውን ግብር መክፈል አለባቸው፡፡

  ለ) የደረጃ “ለ” አዲስ ግብር ከፋዮች ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሐምሌ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ግብሩን መክፈል አለባቸው።

አንቀጽ 92/97 በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት

የአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክል፡-

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** ከጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ በስተቀር ማንኛውም ድርጅት፣ የመንግስት መስሪያቤት፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት፣ ወይንም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ለሚከተሉት ግብይቶች ከሚፈፅሙት ጠቅላላ ክፍያ ላይ 3% (ሶስት በመቶ) ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፤-

  ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ግዜ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት የሚፈጸም ክፍያ፤

  ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ አገልግሎት አቅርቦት ውል ከብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) በላይ የሚፈፀም ክፍያ፤

አንቀጽ 92/97 በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት.....የቀጠለ

የአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 4 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 4 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀጽ (4) ተተክቷል፤

- **ንዑስ አንቀጽ (4)፡-** የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ የሚሆንበት አቅራቢ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን እና የታደሰ ንግድ ፈቃድን ያልሰጠ እንደሆነ ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ 30% (ሰላሳ በመቶ) ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 105 የገቢ ግብር ማበረታቻ እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡ የገቢ ግብር ነፃ መብቶች አፈፃፀም

ከአዋጁ አንቀጽ 99 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 104 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 105 ተጨምሯል፤

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** በኢንቨስትመንት ሕጉ መሰረት ኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ኢንቨስተሮች ሊሰጣቸው የሚገባው የገቢ ግብር ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው መሰረት መሆን አለበት።
- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** በዚህ አዋጅና አዋጁን መሰረት በማድረግ በሚወጣው ደንብ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ከተሰጡ የገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብቶች ውጭ የተሰጡ ማናቸውም ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብቶች በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም፣ በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ በተደነገገው መሰረት ማህበሩ በሚያገኘው የንግድ ሥራ ገቢ ላይ የገቢ ግብር ተፈፃሚ አይሆንበትም።

አንቀጽ 100/106 የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ከአዋጁ አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 106 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (መ) ተጨምሯል፤

- **ንዑስ አንቀጽ (1) (መ)፡-** የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 እና ማሻሻያዎቹ፤

መግለጫ

ከአንቀጽ 22 ጀምሮ እስከ አንቀጽ 102 ድረስ ያሉት የነባሩ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 22 እስከ 108 በሚል ተስተካክለዋል፡

አንቀጽ 101/107 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከሚሆንበት የግብር አመት በፊት ላለው የግብር አመት ያልተሰበሰበ ግብርን

በተመለከተ ከመሻሻሉ በፊት የነበረው የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች እና የተሻረው የተርን ኦቨር ታክስ

አዋጅ ተፈጻሚነት ይቀጥላል፡፡

አንቀጽ 102/108 አዋጁ የሚጸናበት ቀን

ይህ አዋጅ ከሚከተለው ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፦

- **ንዑስ አንቀጽ (1)፡-** በዚህ አዋጅ የተጣለው አማራጭ አነስተኛ ግብር ከሃምሌ 1ቀን 2017 አ.ም ጀምሮ **በሚሰበሰብ ግብር ላይ** ተፈጻሚ ይሆናል፤
- **ንዑስ አንቀጽ (2)፡-** በሰንጠረዥ "መ" መሰረት የሚሰበሰብ ግብር እና በተሸጋሸገው አንቀጽ 97 መሰረት ከግብይቶች ላይ ተቀናሽ የሚደረገው ግብር ከነሃሴ 1 ቀን 2017 አ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፤
- **ንዑስ አንቀጽ (3)፡-** በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች የዚህ የማሻሻያ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ከሀምሌ 1 ቀን ጅምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ይሆናል።

እናመሰግናለን!!!